ቁጥር ጠ/0-766/መ-17
Ref. no
06/07/ 2015ዓ.ም
Date

ለ _____ ዞን ፍትህ መምሪያ/ቋሚ ምድብ ጽ/ቤት

በየአድራሻቸዉ

ጉዳዩ፡- የተሻሻለዉን የዐቃብያነ ህግ የደረጃ እድገት መመሪያ ስለመላክ፣

ከዚህ ቀደም በስራ ላይ በነበረዉ በተሻሻለዉ የዐቃብያነ ህግ የደረጃ እድገት መመሪያ በአፈጻጸም የተስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላትና የደረጃ እድገት አሰጣጡ በግልጽ መስፈርት ላይ የተመሠረተ እና ወጥነት ያለዉ እንዲሆን በማድረግ ዐቃብያነ ህግና ሌሎች የህግ ባለሙያዎችን ማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ በስራ ላይ የነበረዉ መመሪያ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት የተዘጋጀዉ ረቂቅ የዐቃብያነ ህግ የደረጃ እድገት ማሻሻያ መመሪያ በክልሉ የዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ዉይይት ከተደረገበት በኋላ ከየካቲት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ ተወስኗል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በወሰነዉ መሠረት ከየካቲት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ እያሳሰብሁ፣ የተሻሻለዉን የክልሉ ዐቃብያነ ህግ የደረጃ እድገት መመሪያ ቁጥር 22/2015 ዓ.ም 26 ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን አስታዉቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገረመው ገብረጻድቅ መላኩ
ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለም/ቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለዐቃብያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ጽ/ቤት

ፍትህ ቢሮ



☎ 058-220-09-17 Fax No. 058-220-36-29 P.o.Box 995
Email:- anrsattorneygeneral2019@gmail.com

# መመሪያ ቁጥር 21/2015 ዓ.ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ የተሻሻለዉ የዐቃብያነ-ሕግ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ መመሪያ

በክልልም ሆነ በዞን ደረጃ በሚገኙ የዐቃብያነ ሕግ ክፍት መደቦች ዐቃብያነ ሕግ እና ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችን የሚያሳትፍ፣ በግልፅ መስፈርት ላይ የተመሠረተ እና ወጥነት ያለው የደረጃ ዕድገት አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ዐቃብያነ-ሕግ እና ሌሎች ሕግ ባለሙያዎች የትምህርት ዝግጅት፣ አገልግሎት፣ የሥራ አፈጻጸም እና ሌሎች መስፈርትን ሲያሟሉ የደረጃ እድገት እንዲያገኙ ማድረግ የበለጠ እንዲበረታቱ ከማድረጉም በላይ የተቋሙን ውጤታማነትም እንደሚያሳድግ በመታመኑ፤

የደረጃ ዕድገቱን የሚመራ፣ የሚከታተል እና የተለያዩ ቅሬታዎች ሲነሱም መርምሮ የሚወስን አካል መሰየምና አሰራሩን ተቋማዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የክልሉ የዐቃብያነ-ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በተሻሻለው የዐቃብያነ-ሕግ መተዳደሪያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 52/1999 ዓ.ም አንቀፅ 101 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "የተሻሻለዉ የዐቃብያነ-ሕግ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 21/2015 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

(1) **"ደንብ"** ማለት የተሻሻለው የዐቃብያነ-ሕግ መተዳደሪያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 52/1999 ዓ.ም ነው፤

(2) **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ ሲሆን በየደረጃው ያሉ መዋቅሮችንም ይጨምራል፤

(3) **"ዋና ጉባኤ"** ማለት የአብክመ ዐቃብያነ-ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ነው፤

(4) **"ንዑስ ጉባኤ"** ማለት እንደአግባቡ በዞን /በብሄረሰብ /ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ አስተዳደር የተቋቋመ የዐቃብያነ-ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ነው፤

(5) **"የሥራ አፈጻጸም ምዘና"** ማለት በየ6 ወሩ በጊዜ፣ በጥራት፣ በመጠን እና በሌላም መለኪያ የተገኘ የሥራ ክንውን ቀደም ሲል ከተዘጋጀ የአፈጻጸም ግብ ተኮር እቅድ እና የባህሪ ብቃት መገለጫዎች እቅድ ጋር በማነፃፀር የዓቃቤ-ሕጉን የስራ አፈጻጸም ውጤት መለካትና መመዘን ነው፤

(6) **"የትምህርት ዝግጅት"** ማለት በሕግ እውቅና ከተሰጠው የትምህርት ተቋም ወይም ዩኒቨርሲቲ በሚሰጥ ስልጠና የተገኘ የሕግ ሰርቲፊኬት ወይም ዲፕሎማ ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም LLM እና ከዚያ በላይ ወይም በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪና ከሕግ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የትምህርት መስኮች MA እና ከዚያ በላይ ያለው ሆኖ በሕግ ሙያ መሠልጠኑን የሚያሳይ የትምህርት ማስረጃ ነው፤

(7) **"አገልግሎት"** ማለት በሕግ ሙያ ሰልጥኖ በዐቃቤ ሕግነት፣ በዳኝነት፣ በሕግ አሰልጣኝነት፣ በሕግ ተመራማሪነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት፣ በጠበቃነት፣ በነገረፈጅነት፣ በሕግ አማካሪነት፣ በሕግ መምህርነት፣ በሬጅስትራርነት፣ በፍርድ መርማሪነት እና በሌሎች መሰል ሙያዎች መሥራቱን የሚያሳይ የሥራ ልምድ ነው፤

Amhara National Regional State Office of the Attorney General

(8) **"የሕግ ባለሙያ"** ማለት በሕግ ሙያ ከስድስት ወር ያላነሰ ጊዜ ሰልጥኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ከተዘረዘሩ የሕግ ሙያዎች መካከል በአንዱ እየሠራ የሚገኝ የሕግ ባለሙያ ነው፤

(9) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

(10) በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቢሮውና በተዋረድ መዋቅሮች ተሹመው በሚያገለግሉ ዐቃብያነ-ሕግ፣ በዞን ፍትሕ መምሪያ፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች እንዲሁም የመመሪያውን መሰፈርት አሟልተው በውድድሩ በሚሳተፉ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ፡-

(1) ዐቃብያነ-ሕግ መልካም የሆነ የአገልጋይነት መንፈስ ተላብሰው እንዲሠሩ ግልጽ የሆነ መወዳደሪያ መስፈርት እንዲኖር በማድረግ የሥራ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ማስቻል፤ እና

(2) ብቃት ያላቸውን የሕግ ባለሙያዎች አወዳድሮ ወደ ቢሮው በማምጣት ቢሮው የተቋቋመበትን ዓላማ በውጤታማነት ማሳካት ነው።

## 5. ለውድድር ብቁ የማያደርጉ ሁኔታዎች

(1) በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ተከሶ የተቀጣና የተወሰነበትን የቅጣት ጊዜ ጨርሶ አንድ ዓመት ከስድስት ወር፤ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ተከሶ የተቀጣና የተወሰነበትን የቅጣት ጊዜ ጨርሶ ሶስት ዓመት ያላለፈው፤

(2) ለአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ በመደበኛ ትምህርት ወይም በስልጠና ምክንያት ከመደበኛ ሥራው ተለይቶ በትምህርት ወይም በስልጠና ላይ የሚገኝ፤

(3) በሥራ አፈፃፀሙ ከአጥጋቢ በታች ያገኘ፤

(4) ጡረታ ሊወጣ የአንድ ዓመት ጊዜ የቀረው፤

የደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪ አይሆንም።

## ክፍል ሁለት

## የደረጃ ዕድገት አፈጻጸም መሠረታዊ መርሖዎችና ታሳቢ የሚደረጉ ዝርዝር ሁኔታዎች

### 6. የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ መሠረታዊ መርሆዎች

(1) የውድድር መንፈስን የሚያጠናክር፣ ተገቢ ለሆነ የሥራ አፈፃጸም፣ ለመልካም ሥነ-ምግባር፣ ለታታሪነት ሚዛናዊ የሆነ ዋጋ የሚሰጥና ግልፅ የሆነ አሠራር ሥርዓትን መከተል፤

(2) ለአዲሱ የሥራ ኀላፊነት የተወሰነውን ተፈላጊ መስፈርት ማሟላቱንና ኀላፊነቱን ተቀብሎ ለመሥራት የሚኖርን ፈቃደኝነት ያረጋገጠ ዕድገት አሰጣጥ መርሕን ተግባራዊ ማድረግ፤

(3) ፍትሐዊ የሆነ አሠራርን መሠረት ያደረገ የግልጽነትና የተጠያቂነት መርሕን ሥራ ላይ የሚያውል አካሄድን መከተል ማስቻል፤

(4) የዐቃቤ-ሕጉ ወይም ለደረጃ ዕድገት የሚወዳደረው የሕግ ባለሙያ፦

ሀ) ከፍተኛ የሥራ ችሎታና ፍላጎት፣

ለ) አጥጋቢ የሥራ አፈጻጸም ሪከርድ፣

ሐ) መልካም ሥነ-ምግባርና ኃላፊነትን ለመቀበል ያለው ዝግጁነት፣ እና

መ) ለሌሎች አርአያነት የሚኖረውን ፋይዳ ግምት ውስጥ ማስገባት።

### 7. ለደረጃ ዕድገት ውድድር ታሳቢ የሚደረጉ ሁኔታዎች

(1) ለደረጃ ዕድገት የሚወዳደረው የሕግ ባለሙያ ለዞን ዐቃቤ-ሕግነት ደረጃ ዕድገት ካገኘ በኋላ ለሌላ የደረጃ ዕድገት መወዳደር የሚችለው ባደገበት ሥራ መደብ ላይ ቢያንስ ለአራት ዓመት ካገለገለ በኋላ ነው፤

(2) አንድ የወረዳ ዐቃቤ-ሕግ ወደ ዞን ለሚደረግ የደረጃ ዕድገት የሚወዳደረው የቅድመ-ሥራ ሥልጠና ጊዜን ጨምሮ በተመደበበት ደረጃ ቢያንስ ሶስት ዓመት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ ይሆናል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው ቢኖርም የቅድመ-ሥራ ወይም የሥራ ላይ ሥልጠና ወስዶ በሌላ ተቋም ከአምስት ዓመት ያላነሰ ቀጥተኛ አገልግሎት የሌለውን የሕግ ባለሙያን አይመለከትም፤

(4) ዐቃቤ-ሕጉ ወይም ለደረጃ ዕድገት የሚወዳደረው የሕግ ባለሙያ ለውድድር ሲቀርብ በውድድር ለመያዝ የታሰበው የሥራ መደብ ደረጃ የሚጠይቀውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

ስለማሟላቱና በዲሲፕሊን ተከሶ ያልተቀጣ ስለመሆኑ በምዝገባ ወቅት ከሚሠራበት ተቋም ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤

(5) የወንጀል ወይም የዲሲፕሊን ክስ ያለበት ዐቃቤ-ሕግ ወይም የሕግ ባለሙያ ያለበት የወንጀል ወይም የዲሲፕሊን ክስ እስካልተቋጨና ከተጠረጠረበት የወንጀል ወይም የዲሲፕሊን ክስ ነጻ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ለውድድሩ መመዝገብ አይችልም።

## 8. ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ስለሚደረግ ማበረታቻ

(1) ለሴት ተወዳዳሪዎች ካገኙት ነጥብ በተጨማሪ 3 ነጥብ ይደመርላቸዋል፤

(2) ተወዳዳሪዎቹ ሴት አካል ጉዳተኞች ከሆኑ አምስት ነጥብ ይደመርላቸዋል፤

(3) ለአካል ጉዳተኛ ወንድ ተወዳዳሪዎች ካገኙት ነጥብ በተጨማሪ አራት ነጥብ ይደመርላቸዋል።

## 9. ለፍትሕ ጽሕፈት ቤት እና መምሪያ ኃላፊዎች ስለሚደረግ ማበረታቻ

(1) የወረዳ /ከተማ አስተዳደር/ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ወይም የዞን/ብሔረ-ሰብ /አስተዳደር ፍትሕ መምሪያ ኃላፊዎች ሲወዳደሩ ሶስት ነጥብ ይደመርላቸዋል፤

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጠው ነጥብ የሚሰጠው በኃላፊነት እየሠሩ ላሉና ቢያንስ ሶስት ዓመት በዚሁ ኃላፊነት ያገለገሉ ከሆነ ብቻ ነው።

## 10. እኩል ስለሆነ ውጤት

(1) በደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪዎች መካከል የነጥብ እኩልነት ሲኖር፡-

ሀ) የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ድምር ውጤት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል፣

ለ) ይህም ሆኖ እኩል ከመጡ የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል፣

ሐ) ይህም ሆኖ እኩል ከመጡ በአገልግሎት ቀዳሚነት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል፣

መ) ይህም ሆኖ እኩል ከመጡ የተሻለ ውጤት (GPA) ላለው ቅድሚያ ይሰጣል፣

ረ) በዚህ መለየት የማይቻል ከሆነ ለሥራው ቀጥተኛ ቅርበት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል።

## 11. የአገልግሎት አያያዝ ሁኔታ

(1) ዐቃቤ-ሕጉ ወይም ለደረጃ ዕድገት የሚወዳደረው የሕግ ባለሙያ አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ከመደበኛ ሥራው ተነጥሎ በመደበኛ ትምህርት ወይም በስልጠና ላይ ያሳለፈ እንደሆነ ያሳለፈው ጊዜ በአገልግሎት አይያዝለትም፤

(2) በአገልግሎት የሚሰላዉ የሥራ ልምድ በቢሮው የምዝገባ ማስታወቂያ ወጥቶ እስከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን ያለዉ ጊዜ ይሆናል።

## 12. ተወዳዳሪዎችን ስለመጋበዝ

(1) ለዐቃቤ-ሕግ የደረጃ ዕድገት የሚጋበዙ ተወዳዳሪዎች የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) በቢሮው እና በመዋቅሮቹ በማገልገል ላይ የሚገኙ ዐቃብያነ-ሕግ፣ የፍትሕ መምሪያ እና የፍትሕ ጽሕፈት ቤት ኀላፊዎች፣

ለ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በየደረጃው የሚገኙ ዳኞች፣ ፍርድ መርማሪዎች፣ ሬጂስትራሮች እና ተከሳካይ ጠበቆች፣

ሐ) የአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች፣

መ) የዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህራን፣

ሠ) የፍትሕ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም አሰልጣኝና ተመራማሪዎች፣

ረ) የፍትሕ ሚኒስቴር ዐቃብያነ-ሕግ፣

ሰ) ነገረ-ፈጆች፣ የሕግ ኤክስፐርቶች ወይም የሕግ አማካሪዎች፣

ሸ) የሌሎች ክልሎች የዞን ወይም የክልል ዐቃብያነ-ሕግ፣

ቀ) ጠበቆች፤

(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አገላለጽ ቢኖርም ዋና ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በቢሮው መዋቅር የሚገኙ ዐቃብያነ-ሕግን ብቻ በመጋበዝ የደረጃ ዕድገት ውድድር እንዲደረግ ሊወስን ይችላል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚጋበዙ ተወዳዳሪዎች በዚህ መመሪያ የሰፈሩትን ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ አፈፃፀም የሥነ-ምግባር እና የአገልግሎት መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል።

## ክፍል ሦስት

## የደረጃ ዕድገት መወዳደሪያ መስፈርት፣ የነጥብ አሰጣጥ እና የውድድሩ ሂደት ንዑስ ክፍል አንድ መስፈርት

### 13. ስለመወዳደሪያ መስፈርት

ለደረጃ ዕድገት አጠቃላይ የሚያዘው ነጥብ ከ100% ሆኖ የሚከተሉትን አምስት መስፈርት መሠረት በማድረግ ተፈፃሚ ይሆናል፦

(1) የትምህርት ዝግጅት፤

(2) የሥራ አፈጻጸም፤

(3) ሥነ-ምግባር፤

(4) አገልግሎት፤ እና

(5) ፈተና ናቸው።

### 14. የትምህርት ዝግጅት

(1) ለትምህርት ዝግጅት 15% ሆኖ፦

ሀ) ለመጀመሪያ ዲግሪ ----------11%፤

ለ) ለሁለተኛ ዲግሪ ----------13%፤

መ) ለዶክትሬት ዲግሪ ----------15% የሚሰጥ ይሆናል፤

(2) ለዞን እና ለክልል የዐቃብያነ-ሕግ የደረጃ ዕድገት ውድድር ብቁ ለመሆን ዐቃቤ-ሕጉ ወይም ለደረጃ ዕድገት የሚወዳደረው የሕግ ባለሙያ ቢያንስ በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖረው ይገባል፤

(3) የመውጫ ፈተና ውጤት የማቅረብ ግዴታ ያለበት ዐቃቤ-ሕግ እና ለደረጃ ዕድገት የሚወዳደር የሕግ ባለሙያ ምዝገባው ከመጠናቀቁ በፊት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

### 15. የሥራ አፈጻጸም 20%

(1) ለማንኛውም ዉድድር የሚያበቃ ዝቅተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ቢያንስ አጥጋቢ መሆን አለበት፤



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

(2) የመጨረሻዎቹን የሁለት ጊዜ የዉጤት ተኮር እና የባህሪይ ብቃት ዕቅድ ምዘና ዉጤቶችን አማካኝ ውጤት በ 0.2 በማባዛት የሚገኘው ውጤት የሚያዝ ይሆናል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ዉጤቶች አስቀድሞ ያልተሞሉ ከሆነ ወደኋላ ያሉት የመጨረሻ ዉጤቶች ሊያዙ ይገባል፤

(4) በተለያየ ምክንያት የሥራ አፈጻጸም ውጤት መሙላት የማይቻል እንደሆነ የስራ አፈጻጸም ውጤት ሳያስፈልግ በሌሎች መስፈርት የተገኘው ውጤት ድምር ወደ መቶ ፐርሰንት ተቀይሮ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፤

(5) ከፍተኛና በላይ የሆነ የሥራ አፈጻጸም ዉጤት ያገኘ ተወዳዳሪ መስሪያ ቤቱን ለመለወጥ በልዩነት ያስመዘገበዉ ተግባሩና ዉጤቱን በሰጠዉ አካል ማኔጅመንት ተገምግሞና ፀድቆ ከቃለ ጉባኤ ጋር ዉጤቱ በምዝገባ ወቅት ካልቀረበ በስተቀር 79.99% እንዳገኘ የሚቆጠር ይሆናል፤

(6) የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ ከተለጠፈ በኋላ የተሞላ የስራ አፈፃፀም ውጤት ለዉድድር ማቅረብ የተከለከለ ነው።

16. **ሥነ-ምግባር** 15%

በዚህ መመሪያ ከአባሪ 2 እስከ 4 በተቀመጡት ዝርዝር መስፈርት መሠረት በፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ ወይም እንደ አግባብነቱ በዋና ወይም በንዑስ የዐቃብያነ-ሕግ ወይም የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚሞላ ሆኖ ዝርዝር አፈፃፀሙም፡-

(1) አገልግሎት አሰጣጥ 5%፣

(2) ገለልተኝነትና ከደባል ሱስ ነፃ ስለመሆን 5%፣

(3) ታታሪነትና አርአያ መሆን 5 %።

17. **አገልግሎት** 10% ሆኖ፡-

(1) ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት አገልግሎት ላለው 2%፤

(2) ከአምስት ዓመት በላይ እስከ ሰባት ዓመት 4%፤

(3) ከሰባት ዓመት በላይ እስከ ዘጠኝ ዓመት 6%፤

(4) ከዘጠኝ ዓመት በላይ እስከ አስራ አንድ ዓመት 8%፤

(5) ከአስራ አንድ ዓመት በላይ 10%፤

ነጥብ ያገኛል።



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

## 18. በየደረጃዉ ለሚገኙ ዐቃብያነ-ሕግ ወይም የሕግ ባለሙያዎች የደረጃ ዕድገት ውድድር ስለሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

(1) ለዞን ዐቃቤ ሕግ

የሚከተሉትን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ የሕግ ባለሙያ ለዞን ዐቃቤ-ሕግነት ሊወዳደር ይችላል፦

ሀ) በከተማ አስተዳደር ወይም በወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት በዐቃቤ-ሕግነት ሥራ ላይ ያለና ሶስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለዉ፣

ለ) በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሬጂስትራርነት ወይም ተከላካይ ጠበቃነት ወይም በከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት ወይም ፍርድ መርማሪነት እየሠራ ያለ እና አራት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣

ሐ) በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከላካይ ጠበቃነት ወይም ሬጂስትራርነት ወይም በወረዳ ፍርድ ቤት በዳኝነት እየሠራ ያለ እና ስድስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣

መ) በአስተዳደር ፍርድ ቤት በዳኝነት እየሠራ ያለና በከተማ አስተዳደር ወይም በወረዳ በዐቃቤ-ሕግነት ወይም በዳኝነት የሁለት ዓመት አገልግሎት ያለው ሆኖ ስምንት ዓመት ያገለገለ፣

ሠ) በዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህርነት እየሠራ ያለና ሰባት ዓመት ያገለገለ፣

ረ) በሌሎች ክልሎች በዞን ዐቃቤ-ሕግነት ሥራ ላይ ያለና በፍትሕ መምሪያ ደረጃ ሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣

ሰ) በነገረ-ፈጅነት ወይም በሕግ ኤክስፐርትነት ወይም በሕግ አማካሪነት እየሠራ ያለና በከተማ አስተዳደር ወይም በወረዳ በዐቃቤ-ሕግነት ወይም በዳኝነት ቢያንስ ለሁለት ዓመት የሠራ ሆኖ ስምንት ዓመት ያገለገለ፤

(2) ለክልል ዐቃቤ ሕግ

የሚከተሉትን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ የሕግ ባለሙያ ለክልል ዐቃቤ-ሕግነት ሊወዳደር ይችላል፦

ሀ) በፍትሕ መምሪያ በዞን ዐቃቤ-ሕግነት ሥራ ላይ ያለና በፍትሕ መምሪያ ደረጃ አራት ዓመት ያገለገለ፣

ለ) በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ወይም ፍርድ መርማሪነት ሥራ ላይ ያለና በዚሁ ደረጃ አራት ዓመት ያገለገለ፣



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

ሐ) በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሬጂስትራርነት ወይም በተከላካይ ጠበቃነት ወይም በከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ወይም በፍርድ መርማሪነት ሥራ ላይ ያለና በዚሁ ደረጃ ስድስት ዓመት ያገለገለ፣

መ) በአስተዳደር ፍርድ ቤት በዳኝነት ሥራ ላይ እየሠራ ያለና በዞን በዐቃቤ-ሕግነት ወይም በዳኝነት ቢያንስ ለአራት ዓመት የሠራ ሆኖ ስምንት ዓመት ያገለገለ፣

ሠ) በዩኒቨርሲቲ በሕግ መምህርነት እየሠራ ያለና በዞን በዐቃቤ-ሕግነት ወይም በከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኝነት ቢያንስ ለሁለት ዓመት የሠራ ሆኖ በመምህርነት ሙያው አምስት ዓመት ያገለገለ፣

ረ) በፍትሕ ባለሙያዎች ማስልጠኛ ተቋም በአሰልጣኝነት ወይም በተመራማሪነት በሥራ ላይ ያለና በዞን በዐቃቤ-ሕግነት ወይም በከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኝነት ቢያንስ ለሁለት ዓመት የሠራ ሆኖ አምስት ዓመት ያገለገለ፣

ሰ) በክልል ደረጃ በነገረ-ፈጅነት፣ በሕግ ኤክስፐርትነት ወይም በሕግ አማካሪነት እየሠራ ያለና በዞን በዐቃቤ-ሕግነት ወይም በከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኝነት ቢያንስ ለአራት ዓመት የሠራ ሆኖ የአስር ዓመት አገልግሎት ያለው፤

ሸ) በፍትሕ ሚኒስቴር በከፍተኛ ዐቃቤ ሕግነት እና በላይ ስራ ላይ ያለና በዚሁ ደረጃ ሶስት ዓመት ያገለገለ፣

ቀ) በሌሎች ክልሎች ፍትሕ ቢሮ በክልል ዐቃቤ-ሕግነት ሥራ ላይ ያለና በዚሁ ደረጃ ሶስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

በ) በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሠ) ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህርነት እየሠራ ያለና አስራ አንድ ዓመት ያገለገለ፣

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጹት መስፈርት እንደተጠበቁ ሆነው ልዩ የሆነ የሥራ ልምድ፣ ችሎታና ክህሎት የሚጠይቁ እንደ የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት እና መሰል የስራ ክፍል ላይ ሊሠራ የሚችል የሕግ ባለሙያ በደረጃ ዕድገት ማሟላት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የዋና ጉባኤው ሰብሳቢ የአመልካቹን የሕግ ባለሙያ መረጃ አደራጅቶ ለዋና ጉባኤው በማቅረብ ሹመቱን ማስጸደቅ ይችላል፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጡት አገላለጾች ቢኖሩም በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 14 እስከ 17 ያሉትን መስፈርት ያሟሉ ተወዳዳሪዎች ሁሉ ዋና ጉባኤው የሚያዘጋጀውን ፈተና ማለፍ ይጠበቅባቸዋል።



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

19. **ጠበቆች ለዐቃቤ-ሕግ የደረጃ ዕድገት ስለሚጋበዙበት ሁኔታ፣**

(1) ማንኛዉም ጠበቃ በጥብቅና ሥራ ከመሰማራቱ አስቀድሞ በዐቃቤ-ሕግነት ይሠራ ከነበረና ወደነበረበት የቢሮው መዋቅር ተመልሶ በዐቃቤ-ሕግነት ለመሥራት የሚያመለክት ከሆነ ወይም ወደሚቀጥለዉ ደረጃ የቢሮው መዋቅር ለመወዳደር የሚጠይቀዉን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ እንደአግባቡ ወደነበረበት የቢሮው መዋቅር ሊመለስ ወይም በደረጃ ከፍ ወዳለዉ የቢሮው መዋቅር ለማገልገል ሊወዳደር ይችላል፤

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠው አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠበቃዉ በዐቃቤ-ሕግነት ለመሥራት ወይም ለመወዳደር ያቀረበዉ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችለዉ ጠበቃዉ ለዐቃቤ-ሕግነት ሥራ የሚስማማ ሥነ-ምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ከሚመለከታቸዉ አካላት የሚያቀርበዉን ማስረጃ ዋና ጉባዔው መርምሮ ሲቀበለዉ ብቻ ይሆናል።

20. **ወደ ዐቃቤ ሕግነት ለመመለስ ስለሚቀርብ ጥያቄ**

በቢሮው መዋቅር በዐቃቤ ሕግነት ሲያገለግል የነበረና በተለያዩ ምክንያቶች ከስራ የለቀቀ ባለሙያ ወደ ቢሮው መዋቅር ለመመለስ ሲያመለክት አሁን እየሰራ ካለበት ተቋም የተሻለ የስራ አፈፃፀም እና ወቅታዊ የስነ-ምግባር ማረጋገጫ ሲያቀርብ ጥያቄው ለዋናው ጉባኤ ቀርቦ ሲወሰን ይሰራበት ወደነበረው የዐቃቤ ሕግነት ደረጃ ያለ ውድድር ሊመደብ ይችላል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለ ፈተና

21. **ፈተና 40% የሚይዝ ሲሆን፦**

(1) ዐቃቤ-ሕጉ ወይም ወደ ቢሮው የሚገባው ባለሙያ ለውድድር ቀርቦ በውድድር ለመያዝ የታሰበውየሥራ መደብ ደረጃ የሚጠይቀውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ ማሟላቱ ከተረጋገጠ በኋላ ባገኘው ድምር ውጤት መሠረት ለፈተና ለመቅረብ ይወዳደራል፤

(2) በትምህርት ዝግጅት፣ በሥራ አፈጻጸም፣ በሥነ-ምግባርና በአገልግሎት የተሰጠው 60% በፈተና ከተገኘው 40% ጋር ተደምሮ የተወዳዳሪው የመጨረሻ ውጤት ይሆናል።

## 22.የፈተናዉ ይዘትና አፈፃፀም

(1) በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርት ለሚያሟላ ተወዳዳሪ ፈተና ይሰጣል፤

(2) ለተወዳዳሪው የሚቀርበዉ ፈተና ይዘት ተወዳዳሪው ለዐቃቤ-ሕግነት ሙያ አስፈላጊ የሆነውን፦

ሀ) እውቀት፣

ለ) ክህሎት፣ እና

ሐ) ሥነ-ምግባር፣

የሚመዝን መሆን ይኖርበታል፤

(3) ተወዳዳሪዎችን ለመመዘን የፅሁፍ ፈተና ይሰጣል፤

(4) ለሴቶች እና አካል ጉዳተኞች የሚሰጠውን ተጨማሪ ነጥብ በተመለከተ ከላይ በተጠቀሱት መስፈርት በተገኘው ድምር ውጤት ላይ ተደምሮ የሚያዝላቸው ይሆናል።

# ክፍል አራት

# ስለ ደረጃ ዕድገት ውድድር ማስታወቂያ አወጣጥ፣ አፈጻጸም፣ የነጥብ አሰጣጥና የውጤት አገላለጽ

## 23.ስለደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ አወጣጥ

(1) የደረጃ ዕድገት ውድድር ከመፈጸሙ በፊት በሚመለከታቸው የቢሮው መምሪያዎችና ጽሕፈት ቤቶች በኩል ተወዳዳሪዎች እንዲያውቁት ሲደረግ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ መስፈርት ጭምር ተዘርዝረው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

(2) ለዐቃቤ-ሕግነት የደረጃ ዕድገት የሚወጡ ማስታወቂያዎች በቢሮውና በመዋቅሮቹ የማስታወቂያ ሠሌዳ፣ በኤሌክትሮኒክ መረጃ ማሠራጫዎች እና ሌሎች መረጃ ማሠራጫዎች ይፋ ይደረጋሉ፤

(3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አገላለጽ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ዋና ጉባዔው የውስጥ ማስታወቂያ እንዲወጣ ሊያዝዝይችላል፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ማስታወቂያው የሚከተሉትን ጭምር መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ) ማስታወቂያው የወጣበት ቀን፣ ወርና ዓመተ-ምህረት፣



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

ለ) ቢሮው ዐቃቤ-ሕጉን በቋሚነት ለመመደብ የፈለገበትን ቦታ ወይም የባለሙያ ክፍተት የሚገኝበትን መምሪያ፣

ሐ) በደረጃ ዕድገቱ የሚፈለጉ ዐቃብያነ-ሕግን ብዛት፣

መ) የመመዝገቢያ ቦታና ቀን፣

ሠ) ማስታወቂያውን ያወጣው ክፍል ስም፣ ፊርማና ማህተም፤

(5) የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያው ፈተና ከመከናወኑ አሰር የሥራ ቀናት አስቀድሞ እንዲወጣ ይደረጋል፤

(6) በወጣው ማስታወቂያ መሠረት መወዳደር የሚፈልግ ዐቃቤ-ሕግ ወይም ወደ ቢሮው የሚገባ የሕግ ባለሙያ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከት እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት፤

(7) በበቂ ምክንያት በአካል ተገኝቶ ማመልከቻ ቅፁን ለመሙላት እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ለማቅረብ የማይችል ዐቃቤ-ሕግ ወይም የሕግ ባለሙያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከተውን ሥርዓት በወኪሉ አማካኝነት ሊያከናውን ይችላል።

## 24. የውድድሩ አፈጻጸም ሂደት

(1) ከዐቃቤ-ሕግነት ዉጭ የሚሠሩ ባለሙያዎች ለዐቃቤ-ሕግነት ለመወዳደር ከመመዝገባቸዉ በፊት የዋና ጉባዔ ጽሕፈት ቤቱ እንዲወዳደሩ የሚፈቅድ ቢሆን ከሚሠሩበት መሥሪያ-ቤት በዐቃቤ-ሕግነት ቢሾሙ ተቃዉሞ የሌለዉ ስለመሆኑ የስምምነት ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

(2) ለዞን ወይም ለክልል በሚደረግ የደረጃ ዕድገት ተወዳድሮ ያለፈ ዐቃቤ-ሕግ/የሕግ ባለሙያ ተወዳዳሪ/ እንደአግባብነቱ ቢሮው በሚመድበው ክፍት የሥራ ቦታ የማገልገል ግዴታ አለበት፤

(3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አገላለጽ ከአማርኛ የሥራ ቋንቋ የተለየ የሥራ ቋንቋ በሚጠቀሙ የብሔረሰብ አስተዳደሮች ለመወዳደር የተመዘገቡ ተፈታኞችን የሚመለከት አይሆንም፤

(4) ማንኛውም ተወዳዳሪ ተወዳድሮ ባመጣው ውጤት መሠረት ከተመደበ በኋላ ፈቃደኛ ካልሆነ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት በሚወጡ የደረጃ ዕድገት ውድድሮች መሳተፍ አይችልም፤



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

(5) በማናቸውም የደረጃ ዕድገት ውድድሮች ለእጩ ተወዳዳሪዎች የተጋነነ ነጥብ ተሰጥቷል የሚል ጥርጣሬ በተፈጠረ ጊዜ ማስረጃዎች እንዲላኩ ወይም በአካል ወርዶ እንዲጣራ የሚደረግ ሲሆን ሆን ተብሎ አላግባብ የተሰጠ ነጥብ መኖሩ ከተረጋገጠ የተሰጠው ነጥብ የሚሰረዝ ሆኖ ነጥቡን በሰጠው ኃላፊ ላይም ተጠያቂነትን የሚያስከትል ይሆናል።

(6) በደረጃ እድገት ውድድሩ የተሻለ ነጥብ በማምጣት ካለፉ ተወዳዳሪዎች በተጨማሪ ባስመዘገቡት ውጤት መሰረት ተጠባባቂዎች እንዲኖሩ ይደረጋል፤ የተጠባባቂዎች የቆይታ ጊዜ ሶስት ወር ይሆናል።

(7) በውድድሩ የተሻለ ነጥብ በማምጣት ያለፉ ተወዳዳሪዎች በተለያየ ምክንያት ባለፉበት መደብና ቦታ ስራቸውን መጀመር ካልቻሉ ወይም ውድድሩ በተከናወነበት መደብና ቦታ በተለያየ አጋጣሚ ክፍት መደቦች ከተፈጠሩ እና በተጠባባቂነት የተያዙ ተወዳዳሪዎችን መመደብ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጠባባቂዎች እንዲሾሙ ሊደረግ ይችላል።

## 25. የነጥብ አሰጣጥ ሂደት

(1) በዚህ መመሪያ መሠረት ለትምህርት ዝግጅት፣ ለሥራ አፈጻጸም፣ ለሥነ-ምግባር እና ለአገልግሎት የሚሰጥ ነጥብ በንዑስ ጉባኤ ጽሕፈት ቤቶች ተደራጅቶ ለዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት እንዲላክ ይደረጋል፤

(2) ለዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች ወይም የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች ወይም ቡድን መሪዎች የሚሰጠው የሥራ አፈጻጸም ውጤት በየደረጃው ባሉ የቅርብ ኃላፊዎቻቸው የሚሞላ ይሆናል፤

(3) የጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች የሥራ አፈጻጸም ውጤት በመምሪያ ኃላፊው የሚሞላ ይሆናል፤

(4) ለመምሪያ ኃላፊዎች የሚሰጠው የሥራ አፈጻጸም ውጤት በቢሮ ኃላፊው የሚሞላ ይሆናል።

## 26. ስለ ሹመትና ምደባ

(1) ቢሮው ባወጣው የደረጃ ዕድገት ውድድር ተወዳድሮ ያለፈ ማንኛውም ዐቃቤ-ሕግ ወይም ወደ ቢሮው የሚገባ የሕግ ባለሙያ ወዲያውኑ የደረጃ ዕድገቱ አሸናፊ መሆኑን የሚገልጽ



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

ደብዳቤ ይጻፍለታል፣ ደብዳቤ ከተጻፈለት ጊዜ ጀምሮም አዲሱ ደረጃ የሚያስገኘው ደመወዝ ተጠቃሚ ይሆናል፤

(2) የወረዳ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይም የዞን/የብሄረሰብ/የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/አስተዳደር ዐቃቤ-ሕግ መምሪያ ኃላፊ የነበረ ዐቃቤ-ሕግ ወይም ከሌላ ተቋም የሚመጣ በዚሁ ደረጃ ላይ ያለ ኃላፊ ለደረጃ ዕድገት ተወዳድሮ ያለፈ እንደሆነ የሚያገኘዉ ደመወዝ ለደረጃዉ የተመደበዉን የመነሻ ደመወዝ ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## የደረጃ ዕድገት ፈፃሚ አካል፣ የልዩ ልዩ አካላት ሥልጣንና ተግባር

### 27. ፈፃሚ አካል

የዐቃብያነ-ሕግን የደረጃ ዕድገት ውድድር የሚፈጽመው እና የሚያስፈጽመው የዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ይሆናል።

### 28. የዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

የዋና ጉባኤው ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

(1) ተወዳዳሪ አመልካቾችን ይመዘግባል ወይም ዉክልና በመስጠት እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤

(2) አጠቃላይ የምልመላ ሂደቱን ያስተባብራል፣ ሂደቱ ስላለበት ሁኔታም በየጊዜዉ ለጉባዔዉ ሰብሳቢ ሪፖርት ያቀርባል፤

(3) ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡትን ልዩ ልዩ ማስረጃዎች በዚህ መመሪያ ከተቀመጡት መስፈርት አኳያ ያጣራል፤

(4) በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ያደራጃል፣ በአግባቡ ይይዛል፣ በዋና ጉባዔዉ በተጠየቀ ጊዜ ያቀርባል፤

(5) እንደ ሁኔታው በውስጥ ወይም በውጭ ፈታኝ ፈተና እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ የፈተና አሰጣጥ እና እርማትን ያስተባብራል፤



የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሪያ ቤት
Amhara National Regional State
Office of the Attorney General

(6) የፈተና ዉጤቶችን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፤

(7) አጠቃላይ የዉድድር ዉጤቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለዋና ጉባዔዉ ሰብሳቢ ያቀርባል፤

(8) ከንዑስ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ተመርምሮና ተጣርቶ የሚቀርበውን የተወዳዳሪዎችን የሥራ አፈጻጸም፣ የሥነ-ምግባር፣ የትምህርት ዝግጅትና የአገልግሎት ድምር ውጤት እና ሌሎች ማስረጃዎችን በማደራጀት ይይዛል፣ ያረጋግጣል፣ ይመረምራል፣ ስህተት ካለ እንዲስተካከል ያደርጋል፤

(9) ከወረዳ ወደ ዞን/የብሔረ-ሰብ /የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/ አስተዳደር ወይም ከዞን/የብሄረሰብ /የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/ አስተዳደር ወደ ክልል ከቀረቡት እጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ከ60% ለትምህርት ዝግጅት፣ ለሥራ አፈጻጸም፣ ለሥነ-ምግባር እና ለአገልግሎት ያገኙትን ነጥብ ደምሮ በውጤት ቅደም-ተከተላቸው ከፈተና በፊት አደራጅቶ ይይዛል፤

(10) ከግማሽ በላይ ውጤት ካገኙት መካከል የክፍት መደብ ብዛትን ግምት ውስጥ በማስገባት ለፈተና መቅረብ የሚገባቸውን በውጤት ቅደም-ተከተላቸው መሠረት ሊወስን ይችላል፤

(11) ለተወዳዳሪዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14፣ 15፣ 16 እና 17 መሠረት የተሰጠውን 60% እና በፈተና ያገኙትን 40% በመደመር የተሻለ ውጤት ያመጡ ተወዳዳሪዎችን በቅደም-ተከተል በመለየት የውሳኔ ሀሳቡን ለቢሮ ኃላፊው ያቀርባል።

## 29. የንዑስ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

(1) የተወዳዳሪዎችን የግል ማህደር ይመረምራል፣ በማህደራቸው የተገኘውን ማስረጃ ሕጋዊነትና ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣ ውጤቱንም ለዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ያሳውቃል፤

(2) ተወዳዳሪዎች ያልተያዘላቸው ጠቃሚ ማስረጃ በመኖሩ እንዲያዝላቸው ሲያቀርቡ ወይም ችግር አለበት ብሎ የጣለውን አስተካክለው ሲያቀርቡ በጥንቃቄ መርምሮ መቀበሉን ወይም አለመቀበሉን ለሚመለከተው ዐቃቤ-ሕግ ይገልጻል፣ የተስተካከለውን መረጃ በመመርመር ለዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ያቀርባል፤



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

(3) በዞን/በብሔረ-ሰብ /በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/አስተዳደር መምሪያ ጎላፊ የወረዳ ፍትሕ ጽሕፈት ቤት ጎላፊዎችንና የመምሪያ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችን እንዲሁም በዞን/በብሔረ-ሰብ /በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/ ወይም በወረዳ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የተሞላውን የዞን /የብሔረ-ሰብ /የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/ አስተዳደር እና የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳወይም ንዑስ ወረዳ ዐቃብያነ-ሕግ የሥራ አፈጻጸም ዉጤት ለዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ይልካል፤

(4) ከየወረዳው ተሞልቶ የሚመጣውን የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ዐቃብያነ-ሕግ የሥነ-ምግባር ውጤት መርምሮ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ከትምህርት ዝግጅት፣ ከሥራ አፈፃፀም፣ ከሥነ-ምግባር እና ከአገልግሎት ውጤት ጋር አጠቃልሎ ምዝገባው በተጠናቀቀ አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ይልካል፤

(5) በደረጃ ዕድገት ውድድር ሂደት ላይ ቅሬታ ያለውን ዐቃቤ-ሕግ ተቀብሎ አቤቱታውን በማስተናገድ ውሳኔ ይሰጣል፤

(6) የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ በዞን/በብሄረሰብ /በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ/ አስተዳደር መምሪያዎችና በወረዳ ጽሕፈት ቤቶች ሰሌዳ መለጠፉን ያረጋግጣል፤

(7) ሌሎች ከደረጃ ዕድገት ጋር የተያያዙ ተግባራትን በውክልና ያከናውናል።

## 30. የዋና ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

ዋና ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

(1) የክልሉን ዐቃብያነ-ሕግ የደረጃ እድገት ምልመላ ሥርዓት በበላይነት ይመራል፤

(2) የተሻለ ውጤት አግኝተው ለደረጃው ብቁ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው ተወዳዳሪዎችን በሰብሳቢው ተረጋግጦ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፤

(3) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የምልመላ ሥርዓቱ በንዑስ ጉባኤ እንዲፈፀም ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## 31. የቢሮ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

(1) ለደረጃ ዕድገት ለሚሰጠው ፈተና የውስጥ ወይም የውጭ ፈታኝ ይሰይማል፤

(2) በዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤት የሚቀርበውን የደረጃ ዕድገት ውድድር የውሳኔ ሀሳብ በመመርመር ለዋና ጉባኤው አቅርቦ ያስጸድቃል፤

(3) የዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ በደረጃ ዕድገት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለውን ተወዳዳሪ ተቀብሎ አቤቱታውን በማስተናገድ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 32. ያለአግባብ የተሰጠ የደረጃ ዕድገትን ስለመሰረዝ

(1) የተሳሳተ ማስረጃ በማቅረብ ወይም በማጭበርበር የተገኘ የደረጃ ዕድገት በማናቸውም ጊዜ ይሰረዛል፤

(2) የተሳሳተው ማስረጃ የቀረበው ወይም የማጭበርበር ድርጊቱ የተፈጸመው የዕድገቱ ተጠቃሚ በሆነው ሰው ሆኖ ከተገኘ በዚህ ምክንያት ያገኘውን ጥቅም ወይም ክፍያ የሚመልስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲሲፕሊንም እንዲጠየቅ ይደረጋል፤

(3) የተሳሳተውን ማስረጃ ወይም ማጭበርበሩን እያወቀ በዚሁ ተግባር እንዲጠቀም የፈቀደ ወይም የተባበረ ኃላፊ መኖሩ ከተረጋገጠ በዲሲፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 33. ስለአቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን

(1) በፈተና ሂደቱ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል የደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪ ወይም ይመለከተኛል የሚል ሌላ ሰው ፈተናው በተካሄደ በሶስት የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ አመቺ ሆኖ ባገኘው የመገናኛ ዘዴ ለዋና ጉባኤው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይም ለቢሮ ኃላፊው የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤

(2) በደረጃ ዕድገት ውጤት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ያለው የደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪ ውጤቱ በይፋ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዋና ጉባኤው ጽሕፈት ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤

(3) ዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው በተጠናቀቀ ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ምላሽ መስጠት አለበት፤



(4) በዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ያልረካ ተወዳዳሪ ወይም ይመለከተኛል የሚል ሌላ ሰው የጽሕፈት ቤቱ ምላሽ በደረሰው ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለቢሮ ኃላፊው ማቅረብ ይችላል፤

(5) ቢሮ ኃላፊው ቅሬታው ከቀረበለት በኋላ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ተገቢ ነው የሚለውን ምላሽ መስጠት አለበት፤

(6) በቢሮ ኃላፊው ምላሽ ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ የቢሮ ኀላፊውን ምላሽ ባወቀ ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን አዘጋጅቶ ለዋና ጉባኤው ለማቅረብ ይችላል፤

(7) ዋና ጉባኤው ቅሬታው በደረሰው በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢ ነው የሚለውን ምላሽ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ዋና ጉባኤው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በቢሮ ኃላፊው የተሰጠውን ውሳኔ ካጸናው የመጨረሻ ይሆናል፤

(8) ቅሬታ የቀረበበት የሥራ መደብ ውጤት ቅሬታው ተመርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በዋና ጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ተይዞ ይቆያል።

## 34. ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

(1) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ የተሻሻለው የዐቃብያነ-ሕግ የደረጃ ዕድገት መመሪያ ቁጥር 14/2010 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

(2) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 35. መመሪያውን የማሻሻል ሥልጣን

ዋና ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

## 36. ስለአባሪዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት የተያያዙ አራት ቅፃቅፆች የመመሪያው አካል ሆነው በሚመለከታቸው አካላት እየተሞሉ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ።



Amhara National Regional State Office of the Attorney General

37. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በክልሉ ዐቃቢያነ-ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ከጸደቀበት ከዛሬ የካቲት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ገረመዉ ገብረጻድቅ

የዐቃቢያነ-ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ

ሰብሳቢ

አባሪ 1

## ለአብክመ ፍትሕ ቢሮ ለዐቃቤ-ሕግ የደረጃ ዕድገት የማመልከቻ ቅፅ

### 1. የአመልካች የግል ሁኔታ

1.1 ሙሉ ስም ከነአያት

_____ _____ _____

1.2 የትውልድ ዘመን

ቀን _____ ወር _____ ዓ.ም _____

1.3. የአሁኑ የመኖሪያ አድራሻ

አገር _____ ከተማ _____ ክ/ከተማ _____ ቀበሌ _____

1.4 ፆታ ☐ ሴት ☐ ወንድ

1.5 ዜግነት _____

1.6. ዕድሜ _____

1.7. የቤተሰብ ሁኔታ ያገባ ☐ ያላገባ ☐

1.8. ቋንቋ፡ በቂ፣ ጥሩ፣ በጣም ጥሩ እና እጅግ በጣም ጥሩ በሚል ይገለፅ።

| ቋንቋ | መናገር | መስማት | መፃፍ | ማንበብ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

## 2. የአመልካች የትምህርት ደረጃ መግለጫ

| | የትምህርት ቤቱ/ተቋሙ ስም | የተማሩበት ጊዜ<br>ከ ---- እስከ ---- | ውጤት |
|---|---|---|---|
| የመጀመሪያ ድግሪ | | | |
| ሁለተኛ ዲግሪ | | | |
| ዶክትሬት ዲግሪ | | | |

3. የአመልካች የስራ ልምድ

| የመሥሪያ ቤቱ ሥም | የሠሩበት ጊዜ ከ ---- እስከ------ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ሥራውን የለቀቁበት ምክንያት |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |

4. የሙያ ሥልጠና ተሳትፎ ካለዎት ይጥቀሱ

| ሥልጠናውን የወሰዱበት ተቋም ስም | የስልጠናው ርዕስ | ሥልጠናው የወሰደው ጊዜ ከ - እስከ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

ከዚህ በላይ ያቀረብኩት መግለጫ እውነትና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

የአመልካች ስምና ፊርማ ቀን፣ ወርና ዓ.ም

_____ _____

የአማራ ክልላዊ መንግስት ★ Amhara National Regional Government ★ Office of the Attorney

አባሪ 2

## አገልግሎት አሰጣጥ/5%/

- ከተሰያዩ አካላት/ የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ፣ የዐቃብያነ-ሕግ ወይም የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ወይም ገዐስ ጉባኤ ወይም በተቋሙ ማኔጅመንት እና በተገልጋዮች የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የሚሞላ ነጥብ ነው።
- የተሰጡት አስተያየቶች በሰንጠረዡ በሰፈረዉ የነጥብ ክብደት አኳያ እየተሰኩ ዉጤቱ የሚመዘን ይሆናል።

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዞን | አገልግሎት አሰጣጥ /5%/ | | | | ዉጤት 5% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ተገልጋይን የማስተናገድ ፍላጎት/በትህትና፣ በአኩልነትና በአክብሮት ማስተናገድ / 1.25%/ | የሥራ ላይ ችግር አፈታቱ /1.25%/ | የባለጉዳይን ችግር ባግባቡ ለመረዳት ጥረትማድረግ፣ በሚገባዉ ልክ ነገር ማስጨረስ /1.25% | ሥራን በመጠን፣ በጥራት የመወሰን ብቃት፣ወጭ ቆጣቢነቱ/ 1.25%/ | |
| 1 | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | |

አባሪ 3

## ገለልተኝነትና ከደባል ሱስ ነፃ ስለመሆን /5%/

✓ ከተለያዩ አካላት/ የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ፣ የዐቃብያነ-ሕግ ወይም የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ወይም ንዑስ ጉባኤ ወይም በተቋሙ ማኔጅመንት እና በተገልጋዮች የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የሚሞላ ነጥብ ሆኖ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሰንጠረዡ በተመለከተዉ የነጥብ ክብደት አኳያ እየተመዘነ ዉጤቱ የሚሞላ ይሆናል።

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዞን | ገለልተኝነትና ከአጉል ሱስ የፀዳ /5%/ | | | | ዉጤት 5% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የሰዎችን ሰብዓዊ መብትና ክብር የሚያከብርና የሚያሥከብር /1.25%/ | በመንግስት ስራና በግል ጉዳዮች የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር የሚያደርገው ጥረት /1.25% | የመንግሥትና የሕዝብ ጥቅምን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በሚዛናዊነት ማስተናገድ/ 1.25%/ | ከደባል ሱስ ነፃ ስለመሆን /1.25/ | |
| 1 | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | | |



አባሪ 4

## ታታሪነትና አርአያ መሆን/5%

- ✓ ከተለያዩ አካላት/ የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ፣ የዐቃብያነ-ሕግ ወይም የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ወይም ንዑስ ጉባኤ ወይም በተቋሙ ማኔጅመንት እና በተገልጋዮች የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የሚሞላ ነጥብ ነው።
- ✓ በዚሁ መሠረት ዉጤቱ በሰንጠረዡ በሰፈሩት የነጥብ ክብደት አኳያ እየተመዘነ የሚሞላ ይሆናል።

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዞን | ታታሪነትና አርአያ መሆን /5%/ | | | ዉጤት/ 5% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ከባልደረባ ጋር ተግባብቶ መስራት/ 1.5%/ | የሥራ ታታሪነትና ለሌሎች አርአያ መሆን/ 2%/ | ከአሰባልታና ከቡድንተኝነት የራቀ/1.5%/ | |
| 1 | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | |